የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16th Year No. 10
ADDIS ABABA 14th January, 2010

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፫/፪ሺ፪ ዓ.ም

ከኢኳቶሪያል ጊኒ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስት መንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፭ሺ፩፻፺፪

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 663/2010**

The Reciprocal Promotion and Protection of Investments Agreement with the Republic of Equatorial Guinea Ratification Proclamation Page 5192

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፫/፪ሺ፪

## <u>ከኢኳቶሪያል ጊኒ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ-ሊክ መንግሥትና በኢኳቶሪያል ጊኒ ሪፐብሊክ መን ግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የባለ-ሁለት ወገን ስምምነት ሰኔ ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም በማላቦ የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋዮቹ አገሮች ሕግ መሠረት መፅደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ ከ፴ ቀን በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ ስለተገለጸ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፳፯ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብ-ሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 663/2010.

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON THE RECIPROCAL PROMOTION AND PROTECTION OF INVESTMENTS WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF EQUATORIAL GUINEA</u>

**WHEREAS,** the Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investments between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Equatorial Guinea was signed in Malabo on 11 June 2009;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force 30 days after the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channels and receipt of the last notification letter;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of January, 2010;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 sub article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከኢኳቶሪያል ጊኒ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፷፫/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኢኳቶሪያል ጊኒ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት በኢኳቶሪያል ጊኒ ዋና ከተማ ማላቦ ላይ ሰኔ ፬ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ሥልጣን

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Reciprocal Promotion and Protection of Investments Agreement with the Republic of Equatorial Guinea Ratification Proclamation No. 663/2010."

## 2. Ratification of the Agreement

The Investment Promotion and Reciprocal Protection Agreement signed in Malabo on 11th day of June 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Equatorial Guinea is hereby ratified.

## 3. Power of the Ethiopian Investment Agency

The Ethiopian Investment Agency is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of January , 2010**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**